# ተሟጋች ልዩ ዕትም

የኢፌዲሪ የሕገ-መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በኮቪድ 19 መከሰት እና የአስቸኳይ ግዜ አዋጅ መታወጅ ምክንያት በነሐሴ ወር 2012 ዓ.ም.ሊደረግ ታቅዶ የነበረው ምርጫ በመራዘሙ እና ይህንን ተከትሎ የተነሱትን የህገመንግሥት ጥያቄዎች አስመልክቶ የህግ አስተያየት (Amicus Curiae) እንዲቀርብ ግንቦት 01 ቀን 2012 ዓ.ም. በጠየቀው መሰረት ግንቦት 07 ቀን 2012 ዓ.ም.የቀረበ ነው።

## 1. መግቢያ

አትዮጵያ ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ የመንግስትነት ታሪክ ያላት አገር መሆኑን የተለያዩ የታሪክ ድርሳናት ይገልጻሉ።[1] በዘመናዊት ኢትዮጵያ መንግስታት ሲቀያየሩ የተለያየ የመንግስት አስተዳደር ሥርዓት እየተከተሉ የተለያዩ ህገ መንግስታትን ቀርጸዋል። አሁን በስራ ላይ ያለው ህገ መንግስት ህዳር 29 ቀን 1987 ዓ.ም. በህገ መንግስት ጉባዔ የጸደቀ መሆኑን ህገ መንግስቱ ይናገራል። ህገ መንግስቱ በይዘቱ፤ በአረቃቀቅ እና አጸዳደቅ ሂደቱ እንዲሁም አሳታፊነቱ ላይ የሚነሱ ክርክሮች እና ትችቶች[2] እንዳሉ ሆነው እስካሁን ድረስ ያለው የሀገሪቱ የበላይ ህግ ሲሆን አሁን ላለው የመንግስት ሥልጣን ምንጭም ይህ ህገ መንግስት ነው።

በሥልጣን ላይ ያለው ገዢው የፖለቲካ ፓርቲ ላለፉት 27 ዓመታት በየጊዜው በሚካሄዱ ምርጫዎች የመንግስትነት ስልጣንን የያዘ ሲሆንከምርጫ ሂደቶችና ውጤቶች ጋር በተያያዘ ቅሬታዎች መነሳታቸው አልቀረም። ከ2007 ዓም ምርጫ በኋላ ብዙም ሳይቆይ በአገሪቱ ውስጥ በተንሰራፋው የመልካም አስተዳደር እጦት፣ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰትና የፖለቲካ ምህዳር መጥበብ የተነሳ ህዝባዊ አመጾች በመንግስት ላይ ተቀጣጥለው ገዢው ፓርቲ የአመራርና አደረጃጀት ለውጦችን እንዲያደርግ አስገድ ደውታል። የዲሞክራሲ ተቋማትንና ሕጎችን ለማሻሻል እንዲሁም የፖለቲካ ምህዳሩን ለማስፋት በመንግሥት የተወሰዱት እርምጃዎች በመልካምነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው።

ከነዚህ መልካም ውጤቶች ጎን ለጎን አገሪቷ አይታ በማታውቀው መጠን ብሄርን መሠረት ያደረጉ ግጭቶችንም አስተናግዳለች። እነዚህን ግጭቶችም ተከትሎ ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካ አለመረጋጋት ተከስቷል፤ የሰው ሕይወትና ንብረት ጠፍቷል፤ በርካታ ቁጥር ያለው ሕዝብ ከኖረበት ሥፍራ ተፈናቅሎ በዓለም ከፍተኛውን የአገር ውስጥ ተፈናቃይ ቁጥር አገሪቱ አስተናግዳለች። ምንም እንኳን አገሪቷ በእንደዚህ ዓይነት የፖለቲካ አለመረጋጋት ችግር ውስጥ ብትሆንም መንግሥትና የምርጫ ቦርድ ሕጉ በሚያዘው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት አገራዊ ምርጫ ለማካሄድ ዝግጅት መጀመራቸው ይታወቃል። ምርጫውን ለማከናወንም የተለያዩእርምጃዎች ሲወሰዱ ነበር።ከእነዚህም መካከል የምርጫ ቦርድን እንደገና ማዋቀር፤አዳዲስ የቦርድ አባላትን መሾም፤

1. https://www.britannica.com/place/Ethiopia
2. Tsegaye Regassa, The making & legitimacy of the Eth.Constitution: towards bridging the gap between constitutional design and practice, Feb.2010.

አዲስ የምርጫ ህግ ማጽደቅ፤ የምርጫ ቦርድ የምርጫ ጊዜ ሰሌዳን እና የምርጫ ዝግጅትን ይፋ ማድረግ፤የምርጫ ቦርዱ የተለያዩ የምርጫ ማስፈጸሚያ መመሪያዎችን ማዘጋጀት እና በምርጫው ህግ እና አፈጻጸም ከተለያዩ የፓለቲካ ቡድኖች/ፓርቲዎች ጋር ውይይቶችን ማድረግ ተጠቃሾች ናቸው።[3] ነገር ግን በዓለም አቀፍ ደረጃ የተነሳውን ኮቪድ19 የተባለው ወረርሽን ተከትሎ የፌደራልና የክልል መንግሥታት በወሰዷቸው ሕጋዊ የጥንቃቄ እርምጃዎች የተነሣ የምርጫ ቦርድ ምርጫውን በያዘው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ለማከናወን እንደማይችል ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማሳወቁን ተከትሎ የፖለቲካና የሕግ ችግሮች ተከስተዋል።

## 2. <u>የኮቪድ-19 መከሰት እና ምርጫ መራዘም።</u>

ኮቪድ 19 የተባለው ወረርሽኝ በአጭር ጊዜ በመዛመት የዓለም ሀገራትን እያዳረሰበመምጣቱ ምክንያት የዓለም አቀፉ የጤና ተቋም መጋቢት 2 ቀን 2012 ዓም ወረርሽኙ ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ መሆኑን አውጇል።[4] በተለይ ቫይረሱ ከሰው ወደ ሠው በትንፋሽ እና በንክኪ መዛመቱ በአጭር ግዜ ውሥጥ በዓለም ላይ የተያዙትን ሠዎች ቁጥር ከ4.3 ሚሊዮን በላይ ሲያደርገው የሞቱትንም ከ295 ሺህ በላይ አድርሶታል።[5] በኢትዮጵያም እስከ ግንቦት 6 ቀን 2012 ዓም ድረስ ከ272 ሠዎች በቫይረሱ የተያዙ ሲሆን የ5 ሠዎች ህይወት አልፏል።[6]ወረርሽኙ ከጤና ሥጋትነት አልፎበዲሞክራሲያዊ መብቶች ላይም ተጽእኖ እያሳደረ ይገኛል።

ወረርሽኙን ተከትሎ የተለያዩ መንግስታት ሀገራቸውን በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንዲያስተዳድሩ፤ አለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ የትራንስፓርት አገልግሎቶችን እንዲያቋርጡ፤የሌላ ሀገር ዜጋ ወደ ሀገራቸው እንዳይገባ እንዲከለክሉ፤የገቡ ካሉም ከሁለት ሳምንታት ላላነሰ ጊዜ ተለይተው እንዲቆዩ፤የራሳቸውም ዜጎች በቤታቸው ተወስነው እንዲቀመጡ፤የመንግስት እና የግል ድርጅቶች የሚሰጧቸውን አገልግሎቶች እንዲያቋርጡ፤ ከ53 በላይ ሀገሮች ሀገራዊ እና ክልላዊ ምርጫዎች እንዲያራዝሙ።[7] ለመወሰንተገደዋል። በኢትዮጵያም የክልል አስተዳደሮች እና የፌደራሉ መንግስት የተለያዩ እርምጃዎችን ደረጃ በደረጃ ወስደዋል። የትግራይ ክልል ክልላዊ አስቸኳይ ግዜ አዋጅ[8] ቀድሞ ያወጀ ሲሆን የፌደራል መንግስቱም ሀገራዊ አስቸኳይ ግዜ አዋጅ አውጇል።[9] በአስቸኳይ ግዜ አዋጁም የመንቀሳቀስ መብት፤ የመሰብሰብ መብት፤ ሀይማኖታዊ ስርዐቶችን የማከናወን መብት፤ ፍትህ የማግኘት እና የመሳሰሉት መብቶች ተገድበዋል።[10]

ወረርሽኙን ተከትሎ በመንግሥት እየተወሰዱ ያሉ የጥንቃቄ እርምጃዎች ምርጫ ለማድረግ የማያስችሉ መሆኑን በመግለፅ የምርጫ ቦርድ ጥናት አድርጎ እና ከፓለቲካ ፓርቲዎች ጋር ከተወያየ በኋላ ውሳኔ አሳልፏል። የምርጫ ቦርድ ለሕዝብ ተዋካዮች ምክር ቤት ሁኔታውን በማሳወቅ የመጨረሻ ውሳኔ በምክር ቤቱ እንዲሰጥበት ጠይቋል።

[3] https://ethiopianmonitor.com/tag/election2020/
[4] https://www.who.int/emergencies/diseases/novel-coronavirus-2019
[5] John Hopkins University, may 14 2020
[6] https://www.ephi.gov.et/images/novel_coronavirus/Confirmed-case-Press-release_May-14_Amh-v2.pdfየኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት፤ ግንቦት 6 ቀን 2012
[7] International Foundation for Democracy
[8] https://www.ethiopia-insight.com/2020/04/17/is-tigrays-covid-19-state-of-emergency-constitutional-practical/
[9] https://et.usembassy.gov/alert-tigray-regional-state-enacts-travel-ban-and-other-measures-in-the-fight-against-covid-19-effective-saturday-march-28-2020/
[10] Regulation to execute Stare of Emergency Proclamation No.03/2012,Art 3

መንግሥት (ስራ አስፈጻሚው) ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር አራት አማራጮችን በማቅረብ ውይይት አድርጓል። ከዚህ በተጨማሪም በተላያዩ ወገኖች የተለያዩ ህገ መንግስታዊ ጥያቄዎች ተነስተዋል። በእነዚህ ጥያቄወች ምላሽ ላይም ያለው አቋም የተለያየ ነው። የተነሱት ህገ መንግስታዊ ጥያቄዎችም፤

1. ምርጫ በህገ መንግስታዊ መንገድ ሊራዘም የሚችልባቸው ሁኔታዎች አሉ ወይ?
2. ምርጫው እንዲራዘም በህገ መንግሥቱ መሰረት መወሰን ይቻላል ወይ፤ ምርጫ እንዲራዘም ለመወሰን ስልጣን ያለው ህገ መንግስታዊ አካልስ ማን ነው?
3. ምርጫው በተያዘለት ጊዜ ካልተከናወነ ከመስከረም 30/2013 በኋላ የመንግስት ስልጣን በህገ መንግስታዊ መንገድ ለመያዝ የሚችለው ማን ነው፤ ወይም ምርጫው በተያዘለት ጊዜ ካልተከናወነ ከመስከረም 30/2013 በኃላ ገዢው የፖለቲካ ፓርቲ ህገ መንግስታዊ መንግስት ይሆናል ወይ?

ከላይ የተዘረዘሩትን እና ሌሎችንም ተያያዥ ጉዳዮች መሰረት በማድረግ መንግስት እና የተለያዩ የፓለቲካ ፓርቲዎች የተለያዩአቋሞችን መያዛቸውን አሳውቀዋል። የህግ ባለሙያዎችም ትክክል ነው ያሉትን የመፍትሄ ሀሳብ ይደግፈናል ካሉት ፍልስፍና እና የህገ መንግስት ትርጉም ጋር ጽፈዋል፤ በማህበራዊ እና በመደበኛው ሜዲያም ሀሳባቸውን አጋርተዋል።

## 3. ህገ መንግስታዊ የመፍትሔ ሀሳቦች።

### 3.1. በመንግስት በኩል የቀረቡ የመፍትሄ ሃሳቦች።

መንግስት በተለያዩ የህግ ባለሙያዎች ያስጠናቸውን የመፍትሔ ሳሳቦች በም/ጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ በኩል ለፖለቲካ ፓርቲዎችና ለውይይት አቅርቧል። እነዚህም ህገ መንግስት ማሻሻል፤ አስቸኳይ ጊዜ **<u>አዋጅ፤ ምክር ቤቱን መበተን እና የህገ መንግስት</u>** **ትርጉም መጠየቅ**

የሚሉ አራት የመፍትሄ ሀሳቦች ናቸው።

እነዚህአማራጭ የመፍትሔ ሀሳቦችም ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ቀርበው አባላቱከተወያዩባቸውበኋላ ከሁሉም አማራጮች የተሻለዉ መፍትሄ ጉዳዩ ህገ መንግስት እና ህገ መንግስታዊነትን የሚመለከት ስለሆነ የህገ መንግስት ትርጓሜ መጠየቅ ነው የሚለው በአብላጫ ድምጽ ተወስኗል። በውሳኔው ላይ ተቃውሞ ያላቸው አባላትህገ መንግስቱ ግልጽ ስለሆነ ትርጉም አያስፈልገውም፤ ምርጫ ማራዘምን ህገ መንግስቱ አይፈቅድም በማለት ተከራክረዋል።

### 3.2. ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ አስተያየት እንዲሰጥበት የቀረበው ጥያቄ

የኢፌዲሪ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለጉባዔው ያቀረበው ጥያቄ እንደሚከተለው ይነበባል፤

> “... የቅድመ ምርጫ ዝግጅቶችና ምርጫ በሚደረግበት ወቅት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለማወጅ የሚያስገድድ ሁኔታ ቢከሰት ፣ በዚህም የተነሣ ምርጫ ማድረግ የማይቻል ቢሆን የምርጫ ዘመናቸው ያበቃው የምክር ቤቶች እና የአስፈፃሚው አካል የሥራ ዘመን ምን ይሆናል? ምርጫውስ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ እንዲታወጅ ምክንያት የሆነው ክስተት ከተወገደ በኋላ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ሊከናወን ይገባል? የሚሉት ጥያቄዎች ሕገ-መንግሥቱ ምላሽ አለመስጠቱ የገጠመንን ችግር በመፍታት ረገድ ክፍተት አለበት የሚያስብል ነው። በመሆኑም ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች (አንቀጽ 54(1)፣ አንቀጽ 58(3) እና አንቀጽ 93) ከሕገ መንግስቱ ዓላማና ግቦች እንዲሁም መሠረታዊ መርኖች ጋር በማስተሳሰር በማገናዘብ ትርጉም እንዲሰጣቸው” የሚል ነው

### 3.3. የህግ ባለሙያዎች አስተያየት፡፡

የተወሰኑ የህግ ባለሙያዎች አራቱ አማራጭ ሀሳቦች በመንግስት ከመቅረባቸው በፊት ተመሳሳይ የመፍትሄ ሀሳቦችን የሰነዘሩ[11] ሲሆን ሌሎች ደግሞ መንግስት አማራጭ ሀሳቦቹን ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ካሳወቀ በኋላ የህግ አስተያየታቸውን አጋርተዋል፡፡ አብዛኞቹ ባለሙያዎች ህገ መንግስት ማሻሻል ቢቻል ችግሩን ለመፍታት የተሻለ አማራጭ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን ህገ መንግስት ለማሻሻል ህዝብን ማወያየት አስፈላጊ ነው፡፡ ሥለዚህ አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ህዝብን አወያይቶ የህገ መንግስት ማሻሻያ ማድረግ አይቻልም ብለዋል፡፡ አንዳንዶችም በተለየ ሁኔታ ማሻሻያ ሊደረግ ይገባል በማለት ጽፈዋል፡፡[12]የተወሰኑ ባለሙያዎች ደግሞ ህገ መንግስቱ ላይ በተደነገገው የአስቸኳይ ጊዜ ስልጣን መሰረት በስልጣን ላይ ያለው ፓርቲ የመንግስትነት ስልጣኑን ይዞ ምርጫውን አራዝሞ እስከምርጫው ድረስ ህጋዊ ሆኖ መቀጠል ይችላል በማለት ተከራክረዋል፡፡[13]በዚህ ትርጉም መሰረት የህገ መንግስታዊነት ጥያቄ የለም፡፡ይህም መደምደሚያ ህገ መንግስት በመተርጎም የሚደረስበት ነው በማለት የሚከራከሩት ደግሞ የህገ መንግስት ትርጓሜ መጠየቅን የተሻለው አማራጭ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡[14]የተወሰኑት ደግሞ ምርጫው በተያዘለት ግዜ አለመደረጉ የህግ ጥሰት ነው፤ህገ መንግስቱም ግልጽ ነው ስለዚህ ምርጫው መራዘሙ ህገ መንግስታዊ አይደለም[15] በማለት ሀሳባቸውን ያነሳሉ፡፡

### 3.4. የተለያዩ የፓለቲካ ቡድኖች/ፓርቲዎች አስተያየት፡፡

በሀገሪቱ ያሉ የተለያዩ ፓለቲካ ፓርቲዎች የተለያየ አስተሳሰብ አራምደዋል፡፡ ምርጫውን ማድረግ/አለማራዘም፤ የህገ መንግስት ትርጉም መጠየቅ፤ ህገ መንግስቱን ማሻሻል፤ የሽግግር መንግስት ማቋቋም፤የባለ አደራ መንግስት ማቋቋም፤ ፓርቲዎች ተስብስበው ተመካክረው መወሰን፤ በስልጣን ላይ ያለው ፓርቲ ምርጫ እስከሚደረግበት ግዜ ድረስ መቀጠል የሚሉ ሀሳቦችን አቅርበዋል፡፡

## 4. የኢትዮጵያ የህግ ባለሙያዎች ማኅበር እና የጠበቆች ማኅበር አቋም

በአስቸኳይ ጊዜ ህጉ መሰረት መሰብሰብ ስለማይቻል እና የተሠጠንም ጊዜ አጭር በመሆኑ የማኅበራቱን አባላት በስፋት ማሳተፍ ባይቻልም በስራ አስፈጻሚ እና በተወሰኑ አባላት ዘንድ በመወያየት ከህግ እና ህገ መንግስታዊነት፤ ከዲሞክራሲዊ ስርዓት ግንባታ፤ ከዜጎች በሀገራቸው ጉዳይ ላይ የመሳተፍ እና የመወሰን መብት፤ከመንግስት እና ህገ መንግስታዊ ስርዓት ቀጣይነት፤ ከህግ የበላይነት ማክበር እና ማስከበር፤ የተረጋጋ መንግስት የመኖር ፋይዳ፤ የህዝብ ህይወት እና ደህንነትን ከማረጋገጥ አንጻር ጉዳዮችን በጥንቃቄ መርምረናል፡፡ የተለያዩ ሀገራትንም ተሞክሮ ለማየት የተሞከረ ሲሆን፤በጉዳዩ ላይ የተጻፉ እና የታተሙ ሀሳቦችን ተመልክተናል፡፡

ህገ መንግስት የተለየ ህግ ነው፡፡ ህገ መንግስት የህግም የፓለቲካም ሰነድ ነው፡፡ በዚህም ምክንያቶ የህግ እና የፓለቲካ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ክርክሮች ሲነሱ ህገ መንግስታዊ መፍትሄ መሻት የተለመደ ነው፡፡[16]

---

[11] Addis Standard, Bantayehu Demile, Zemelak Aytenew

[12]Addis Standard,Bantayehu

[13] Addis Fortune, Mulugeta Aregawi

[14]Addis fortune, Ethiopia insightAddis Standard, Solomon, Mamo, Abebe, Adem,Yonatan

[15]Addis Standard, Mehari Tadele

[16]Cloud Lefort,Theories of Constitutional Interpretation,

ለዚህም ነው ህገ መንግስት በየግዜው በህገመንግስታዊ መንገድ ካልተሸሻለ እና ካልተተረጎመ አስፈላጊ ሲሆንም ካልተተካ ዘመን ተሸጋሪ እንደማይሆን የመስኩ ባለሙያዎች የሚስማሙት።[17]የረጅም ዓመታት የህገ መንግሥት ታሪክ ያላቸው ሀገራት ልምድም ይህንኑ ይመሰክራል። ሥለዚህ ህገ መንግስትን በህገመንግስታዊ መንገድ መተርጎም፤ ማሻሻልእንዲሁም መተካት ለህግ ልዕልና እና ለህገ-መንግስታዊ ደሞክራሲ ግንባታ ወሳኝ ነው።[18] በዚህ በያዝነው ጉዳይም ህገ መንግስቱን እና የሚወሰዱትን እርምጃዎች ህገ መንግስታዊነት በሚመለከት የሀሳብ ልዩነቶች መንጸባረቃቸው ጤናማ ነው። እንዲህ አይነቱ ውይይት በእውቀት እና ህግን ብቻ መሰረት በማድረግ ከተደረገ ለህገመንግስታዊ ደሞክራሲያዊ ስርዓት ማደግ ከፍተኛ አስተዋጸኦ ያደርጋል።

የህግ ፍልስፍና ጥልቅ የሆነ እና በዘመናት የዳበረ ከመሆኑም በተጨማሪ አስተሳሰቦቹ (ideals) የማህበረሰብን ፓለቲካዊ፤ ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊ፤ ቴክኖሎጂያዊ እና የመሳሰሉትን ፍላጎቶች እየቀደሙ ወይም እየተከተሉ የሚያድጉ ናቸው። በተረቀቀበት ግዜ ሙሉ የነበረ ህግ ጊዜ እያለፈ ሲሄድ እና ተግባር ላይ ሲውል እንዲሁም በሚከሰቱ ለውጦች እና ፍላጎቶች ጉድለት ሊታይበት ይችላል። ስለሆነም እነዚህን ለውጦች ማስተናገድ የማይችል የታሪክ እስረኛ ከሆነ ለህገ መንግስታዊ ደሞክራሲ እድገት እንቅፋት ስለሚሆን ዘመን አይሻገርም፤የታለመለትንም ግብ አይመታም።[19] ህገ መንግስት ያረቀቁት እና ያጸደቁትን ሰዎች ሀሳብ በመረዳት፤ አጠቃላይ የህገ መንግስት ፍልስፍናን በመከተል እንዲሁም አሁን ቢጸፍ ኖሮ ምንሊሆን ይችል ነበር የሚሉትን እና መሰል የመተርጎሚያ ~~መንገዶችን[20] በመከተል መተርጎም~~ አለበት።

[18]Daniel A. Farbel, Legal Pragmatism and the Constitution.

[19]Frank H. Easterbrook, Originalism and Pragmatism: Pragmatism Role in Constitutional Interpretation.

[20]Kevin M. Stak,the divergence of constitutionaland ሥለዚህ ማህበራቱ ህገ መንግስትን ለመተርጎም ብቸኛው ቅድመ ሁኔታ ህዝብ ነው[21] የሚለውን መርህ በመከተል እንዲሁም የህዝብ ሀሳብ ከሚገለጽባቸው መንገዶች ውስጥ ደግሞ በምክር ቤቶች በተወካዮቻቸው፤ በፓለቲካ ፓርቲዎች እንዲሁም በልሂቃኑ የሚገለጽ ስለሆነ ከላይ እንደተገለጸው በምርጫ መራዘም እና የመንግስት ቀጣይነት ላይ የተለያዩ የህገ መንግስት አረዳዶች የተከሰቱ ስለሆነ በጉዳዩ ላይ የህገ መንግስት ትርጉም መስጠት አስፈላጊ ነው ብለው ያምናሉ።

## 5. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በታወጀበትና ምርጫ ማድረግ ባልተቻለበት ሁኔታ አገር የመምራት ኃላፊነት ያለበት ማነው?

### 5.1. ነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳና የሌሎች አገራት ልምድ

በአለም እና በሀገራችን ህዝብ ጤና እና ህይወት እንዲሁም ኢኮኖሚ ላይ ኮሮና ቫይረስአደጋ ደቅኗል። ምርጫውን ለማካሄድ ህገ መንግስቱ የደነገገው የግዜ ገደብ እና ወረርሽኙን ለመከላከል ሀገራችን በአስቸኳይ ጊዜ ውስጥመሆኗ ተገጣጥሟል። ስለዚህ አማራጮቹ በአስቸኳይ ጊዜ ውስጥ ሆኖ ምርጫ ማድረግ እና ወረርሽኙ የሚያስከትለውን ውጤት መቀበል ወይም ምርጫውን ማራዘም ናቸው። ሁለቱንም ማድረግ ቢቻል መታደል ነበር። ነገር ግን እንደኛ አይነት በገንዘብ እና በቴክኖሎጂ ወደ ጎላ የቀረ ሀገር ቀርቶ የበለጸጉትም ሀገራት ይህንን ለማድረግ ሲሳናቸው ተስተውሏል።[22] በእኛ ሀገር ምርጫ በፓስታ ወይም በኤሌክትሮኒክ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ወይም በሞባይል ማድረግ አይቻልም። ለዚህ አገልግሎት የሚሆን መሰረት ልማት እና የሰለጠነ የሰው ሐይል

[21]William vázquez Irizarry,exception and necessity:The possibility of a general theory of emergency

[22]Internatoional Foundation for Electoral Systems,Elections held and mitigating measures taken during Covid 19

የለም፡፡ ይህንን ለማድረግ የሚያስችል የኢኮኖሚ አቅምም ስለሌለ አማራጭ ሊሆን አይችልም፡፡አንዱን መምረጥ ግዴታ ሆኗል፡፡

በዚህም ምክንያት መንግስት እና ዜጎች ከፊት ለፊታቸው የተደቀነውን የህዝብ ጤና እና ደህንነት እንዲሁም ኢኮኖሚ የሚያወድመውን ወረርሽኝ ለመከላከል እርምጃ እየወሰዱ ነው፡፡ ከነዚህ እርምጃዎች ዋናው በህገ መንግስቱ አንቀጽ 93 መሰረት የአስቸኳይ ግዜ አዋጅ በመንግሥት መታወጁ ነው፡፡ ወረርሽኙን ለመከላከል የአስቸኳይ ግዜ አዋጅ ሲታወጅ በሚኒስትሮች ም/ቤት፤ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላትም ሆነ ሌላ የፓለቲካ ሀይል ልዩነት አልነበረም ፡፡ ምክር ቤቱም በአንድ ድምጸ ተአቅቦ በሙሉ ደምጽ ነው የወሰነው፡፡ ሆኖም ሀገራችን በወረርሽኙ ምክንያት በአስቸኳይ ግዜ እየተዳደረች በመሆኗና ምርጫ ለማከናወን የሚያስፈልጉ ቅድመ ዝግጅቶችን ለማድረግ አለመቻሉን የምርጫ ቦርድ ሲያሳውቅና ይህንን ተከትሎም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሕገ መንግሥቱ እንዲተረጎም ጥያቄ ሲያቀርብ ምርጫው “ይራዘም/አይራዘም” በሚለው ላይ ልዩነቶች ተከስተዋል፡፡

ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ከሚገነባባቸው መንገዶች አንዱ የሆነው የውክልና ወይም የምርጫ ዲሞክራሲ ህገ መንግስታዊ ደሞክራሲ ለማጎልበት ከፍተኛ ሚና ያለው ሲሆን ሀገራችንን ጨምሮ በብዙ ሀገሮች ህገመንግስት እውቅና የተሰጠው የዲሞክራሲ ስርዓት ነው፡፡ ብዙ ሀገራት በህገ መንግስታቸው በደነገጉት መሰረት ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የማካሄድ ግዴታአለባቸው፡፡[23]ምርጫ የዜጎች ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ እና ሉዐላዊነትም መገለጫ ነው፡፡[24] ምርጫው በተወሰነው ግዜ መደረጉ ብቻ ሳይሆን ሂደቱ እና የዜጎች በነጻነት እና በብዛት የመሳተፍ መጠን የምርጫውን ተአማኒነት ለማረጋገጥ ወሳኝ ነው፡፡

መደበኛ ምርጫን በህገ መንግስት መሰረት ማከናወን ለዘመናዊ የውክልና ዲሞክራሲ ወሳኝ ኩነት ሲሆን ይህ እድልም ለአንድ መራጭ ዜጋ በአምስት አመት አንድ ግዜ[25] ስለሚያስተዳድሩት ሰዎች(ፓርቲዎች) ሀሳቡን የሚገልጽበት በመሆኑ ትልቅ ግምት የሚሰጠው ነው፡፡

አሁን የገጠመን የህዝብ ጤንነት፤የመንግስት ቀጣይነት እና ምርጫን አጣጥሞ የመሄድ ጥያቄ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ዓለምአቀፋዊ ነው፡፡ ምርጫ ከሌሎቹ መብቶች ተለይቶ በበሽታው ምክንያት ተጽእኖ የማይደርስበት አይደለም፡፡ እንደሌሎቹ መብቶቻችን ሁሉ ወረርሽኙ የዲሞክራሲ መብታችንንም ማወኩ አልቀረም፡፡ በተለይም ምርጫ የምርጫ ቅስቀሳ፤ ሰላማዊ ሰልፍ፤ የአዳራሽ ውስጥ ስብሰባ፤ የቤት ለቤት ቅስቀሳ፤ የሲቪክ እና ሙያ ማህበራት ተሳትፎ፤ የምርጫ ስልጠና፤ የአገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር የምርጫ ታዛቢዎች፤ የመራጩን በንቃት መሳተፍ እና በነጻነት ወጥቶ መምረጥ መቻል የሚጠይቅ ስኬታማነቱም በነዚህ እና መሰል መስፈርቶች የሚመዘን ነው፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ እነዚህን ማድረግ ቫይረሱን በከፍተኛ ሁኔታ ያስፋፋዋል፡፡ ምርጫው ይራዘም አይራዘም የሚለው ክርክር የምርጫውን ፎርም ብቻ ሳይሆን በህገ መንግስቱ መሰረት ነጻ እና ተአማኒነት ያለው መሆንን ታሳቢ ማድረግ አለበት፡፡ ምርጫ በተረጋጋ ሁኔታ በህግ እና በስርዐት ካልተመራ አገርን ሊያፈርስ እና ደሞክራሲንም ሊገድል ይችላል፡፡ በአለምም ሆነ በኛ ሀገር እንደዚህ አይነት ምርጫዎች ለሰው ልጆች ህይወት ማለፍ፤አካል መጉደል፤ ነጻነት ማጣት እና ንበረት መውደምም ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ስለዚህ ምርጫን በዚህ ወቅት ለማድረግ እነዚህን ውጤቶች ሊያመጣ እንደሚችል መገመት ይገባል፡፡

[23]International Electoral Standards Guide Lines for reviewing the legal frame work for elections.
[24]FDRE Constitution Art 8(3)
[25]FDRE Constitution Art 8(3)

ሀገራት የሽብር ጥቃት ሲደርስባቸው፤ በተፈጥሮ አደጋ ሲመቱ ወይም ለተለያዩ ወረርሽኞች ሰለባ ሲሆኑ እና በዚህም ምክንያት ትክክለኛ ምርጫን ለማድረግ ሳይችሉ ሲቀሩ ምን አይነት እርምጃ መውሰድ ይገባቸዋልየሚለውን አማራጭ በሚመለከት የተለያዩ ፅሃፍት የህግ ክፍተት እንዳለ ይገልፃሉ።[26] በዚህ ምክንያት ህገ መንግስት ምርጫ የሚራዘምባቸውን ሁኔታዎች እና ሲራዘም የሚያስከትለውን ውጤትበግልጽ እንዲደነግግ ይመከራል።[27]ነገር ግን ህጉ የህዝቡን የመምረጥ/መመረጥ መብት የማይጋፉ እንዲሆን ተደርጎ ለወቅታዊ ሁኔታዎች ምላሽ ሊሰጥ በሚችል አግባብ መቀረፅ ይኖርበታል።[28]

እኤአ መስከረም 11 ቀን 2001 ዓ.ም. የሽብር ጥቃት በኒዮርክ የደረሰው በግዛቲቱ ምርጫ በሚካሄድበት እለት ነበር።[29] በተመሳሳይ በደቡብ ምስራቃዊ አሜሪካ የሃሪኬን አደጋ የተከሰተው የአውራጃ ምርጫዎች በሚካሄዱበት ወቅት ነበር። የእነዚህ የአስተዳደር ክልሎች ህጎች በምርጫ ጊዜ የተፈጥሮ አደጋ ቢደርስ ወይም የሽብር ጥቃት ቢፈፀም እና ምርጫውን ለማካሄድ ቅድመ ሁኔታዎች የሚሟሉበት ሁኔታ ባይኖር የምርጫው እጣ ፈንታ ምን ይሆናል የሚለውን በሚመለከት የህግ ድንጋጌዎች የሏቸውም። አንዳንድ ሀገራት የተፈጥሮ አደጋ ሲደርስ ወይም የሽብር ጥቃት ሲፈፀም የዜጎችን ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ ለሚወስዷቸው እርምጃዎች የህግ ማዕቀፍ ከማስቀመጥ በዘለለ የምርጫ እጣ ፈንታን የሚወስኑበት የህግ አግባብ የላቸውም። በዚህ ምክንያት ሀገራት የሽብር ጥቃት እና የተፈጥሮ አደጋ ሲደርስባቸው በቅርብ ያቀዱትን የምርጫ ሂደት በተመለከተ ውሳኔ ለመስጠት ሲቸገሩ ማየት የተለመደ ነው።[30]

በተለይም ግልጽ ምርጫ የማራዘም ድንጋጌ በሌለበት ሁኔታ ውሳኔያቸው ከስልጣናቸው ያለፈ ነው፤ ፖለቲካዊ አጀንዳ ያለው ነው፤ አላስፈላጊ በሆነ ሁኔታ የመራጩን መብት የሚያጣብብነው ለሚሉ ትችቶች ሰለባ ይሆናሉ።[31]በእኛም ሀገር አሁን የተከሰተው ተመሳሳይ ችግር ነው። ይሄም ወደህገ-መንግስታዊ ትርጉም እና ወደ ፍርድ ቤቶች ሙግት ይመራል። ከላይ ባነሳናቸው ሁለት የአሜሪካ ጉዳዮች ላይ ተቀራራቢ ውሳኔዎች ተስጥተዋል። በኒውዮርክ ጉዳይ ላይ በወቅቱ የኒውዮርክ የምርጫ ቦርድ የኒውዮርክ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመቅረብ ምርጫው እንዲራዘም ጥያቄ በማቅረብ ምርጫውን አራዝመዋል። በውሳኔያቸው ላይ እንደገለፁት ምርጫው በተፈጠረው ሁኔታ ምክንያት በህጉ መሰረት መካሄድ ስለማይችል መራዘም እንዳለበት ገልጧል። ከውሳኔው በኋላ የወቅቱ የኒውዮርክ ገዥ የነበሩት ሰው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በማወጅ ሁሉንም ምርጫዎች አራዝመዋል።በደቡብ ምሳራቃዊ የአሜሪካ ግዛት እኤአ በኦገስት 29 2005 ዓ/ም በሉዚያና ግዛትኒውኦሪሌንስበደረሰው የሃሪኬን አደጋ ሳቢያ የወቅቱ ገዥ የነበሩት ሰው በተመሳሳይ መልኩ ሊካሄድ የነበረውን ምርጫ ላልተወሰነ ጊዜ አራዝመዋል።

ከዚህ በተለየ ሁኔታ በአስቸኳይ ግዜ አዋጅ ላይ የዳበረ የህግ ፍልስፍና ያላቸው ጀርመኖች ሲሆኑ ሀንጋሪም በዚህ ረገድ የተሻለ ተሞክሮ ካላቸው ሀገራት አንዷ ነች። በእነዚህ ሀገራትህገመንግስት በአስቸኳይ ግዜ የመንግስት ተቋማትን ቀጣይነት ለማረጋገጥ በማሰብ በግልጽምክር ቤትን መበተን እና የስልጣን የጊዜ ገደብ የሚመለከቱ ህግጋትን ተፈጻሚነትን ይገድባል።[32] በተለይ የሀንጋሪ ህገ መንግስት ግልጽ ድንጋጌን ያስቀመጠ ነው። በፈረረንሳይም ግልጽ ድንጋጌ አለ። እነዚህ ሀገራት በዚህ ረገድ የዳበረ ፍልስፍና ያላቸው ናቸው።

[26]Tom Wheeler, Voting in a time of emergency.
[27]Michael T. Morley, Election Emergencies; voting in the Wake of Natural Disasters and Terrorist Attacks, Emory Law Journal
[28]see supra note 27
[29]see supra note 27
[30]see supra note 27
[31]see supra note 27
[32] Andras Jakob , German Constitutional Law and Doctrine on State of Emergency-Paradigms and Dilemmas of a raditional(Continental Discourse),

ከተጻፈው ህገ መንግሥት በፊትም ሀገር፤ህዝብ እና መንግስት ነበሩ። የተጻፈው ህገ መንግስት እነዚህን ለማጠናከር እና ዲሞክራሲያዊ ለማድረግ እንጅ ሊያጠፋቸው አይገባም የሚል ፍልስፍናን ይከተላሉ።[33] የተወሰኑት እንዳውም መንግሥት እነዚህ በአደጋ ላይ ሲሆኑ ራሱን ማፈረስ/መበተን ሊፈቀድለት አይገባም ብለው ደንግገዋል። ሥለዚህ በአስቸኳይ (emergency) ግዜ የመንግስትን ቀጣይነት ማረጋገጥ ህገ መንግስታዊ ነው በማለት በህገ መንግስታቸው ላይ አካተውታል።

### 5.2. የኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ 54(1) እና አንቀፅ 58(3)

ከላይ እንዳየነው የምርጫ ዲሞክራሲ ለሀገር አስተዳድር ወሳኝ ጽንሰ ሃሳብ በመሆኑ ምርጫዎች በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ መካሄድ አለባቸው። የኢትዮጵያም ህገ መንግስት በዚህ ረገድ ግልጽ ነው። ይሁን እንጅ ሀገራት በተለያዩ ሰው ሰራሽ እና የተፈጥሮ አደጋዎች ሲጋለጡ እና የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሲያውጁ ግልፅ ህግ በሌለበት ሁኔታም ጭምር ከተለያዩ ሀገር ልምዶች እንደምናየው ምርጫ የሀገር ህልውናን እና የህዝብ ደህንነትን የሚተካ ወይም የምርጫ ግዜን ማራዘም ከህገ መንግስት እና መንግስት ቀጠይነት እንዲሁም ከህዝብ ጤና የሚበልጥ ባለመሆኑ ምርጫዎች ሲሰረዙ እና ሲራዘሙ አይተናል። ሀገራችን አሁን ካለችበት አጣብቂኝ ሁኔታ አንፃር የህገ-መንግስቱን ድንጋጌዎች ከላይ በዝርዝር በተቀመጡት ሀሳቦች መሰረት መተርጎም ተገቢ ነው።

የኢፌዲሪ ህገ መንግስት በመግቢያው ላይ በግልፅ እንዳስቀመጠው የህገ መንግስቱ ዋና ግብ በሀገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ዘላቂ ሰላም፤ ዋስትና ያለው ዲሞክራሲ እንዲሰፍን፤ ኢኮኖሚዊና ማህበራዊ እድገት እንዲፋጠን በማሰብ የተቀረፀ እንደሆነ ተቀምጧል። መንግሥቱም ፓርላሜንታዊ ነው።ስለዚህም በዚህ ህገ-መንግስት መሰረት ከተቋቋሙት ሦስቱ የመንግሥት ዋና ዋና አካላት ውስጥ በግንባር ቀደምነት የሚጠቀሰው የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ነው። ም/ቤቱ ከአስፈጻሚ አካሉ እና ከህግ ተርጓሚው ጋር በመሆን መንግስት ሆኖ የተቋቋመ ነው። ይህ ተቋም በህገ-መንግስቱ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ያለው ሲሆን ብዙውን ጊዜ የዚህ ተቋም ህልውና ከመንግስት ህልውና ጋር የተቆራኘ ነው።በህገ መንግስቱ አንቀፅ 50(3) መሰረት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፌደራሉ መንግስት ከፍተኛው የሥልጣን አካል ነው። በአንቀፅ 54(1) መሰረት የዚህ ተቋም አባላት ሁሉን አቀፍ፤ ነፃ፤ ቀጥተኛ፤ ትክክለኛ በሆነና ድምፅበሚስጥር በሚሰጥበት ሥርዓት በየአምስት ዓመቱ በህዝብ እንደሚመረጡ ይደነግጋል።

ይሁን እንጂ ይህ ህገ-መንግስት ከላይ የተጠቀሰውበየአምስት ዓመት ምርጫ የማካሄድ ግዴታዎች የሚራዘሙበትንም ይሁን የሚሰረዙበትን ሁኔታ በግልጽ አይደነግግም። ምርጫውቢዘገይ ወይም ባይካሄድ የምክር ቤቱ እጣ ፈንታ ምን ይሆናል የሚለውን ምላሽ የሚሰጥ ግልጽ የተጻፈ ድንጋጌ አላካተተም፤ ከዚህም ባለፈ ሀገሪቱ በተለያዩ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ምክንያት በአስቸኳይ ግዜ አዋጅ ስር ብትሆን እና የዚህን ምክር ቤት አበላት ምርጫ ማካሄድ የማትችልበት ሁኔታ ቢፈጠር ጉዳዩን የሚመለከት ግልጽ ድንጋጌ በህገ-መንግስቱ አልተቀመጠም። በተጨማሪም በሀገሪቱ ሰው ሰራሽ ወይም የተፈጥሮ አደጋ ምክንያት ከፍተኛ ቁጥር ያለው ተመራጭ እና ከፍተኛ የመንግስት ሀላፊዎች ላይአደጋ ቢደርስ ክፍተቱ እንዴት እንደሚሞላ አይደነግግም።

[33]supra note.32

ምርጫ በህገ መንግሥታዊ መንገድ ለማራዘም እንደሚቻል ከላይ የጠቀስናቸው ዓለም ዐቀፋዊ ተሞክሮዎች እና የህግ ፍልስፍናዎች ያረጋግጣሉ። በአሁኑ ወቅት ኮቪድ 19 በተባለው አለም አቀፋዊ ወረርሽኝ ምክንያት 53 ሀገራት የተለያዩ ምርጫዎችን ያራዘሙ ሲሆን በአሜሪካም ከ26 ያላነሱ ግዛቶች ምርጫቸውን አራዝመዋል ወይም በአካል የሚደረግ ምርጫን አግደዋል።[34]ግልጽ ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ ያላቸው ሀገራት ህገ መንግስታቸውን ተጠቅመው ያራዘሙ ሲሆን ግልጽ ድንጋጌ የሌላቸው ደግም በአስገዳጅ ሁኔታ መርህ(Doctrine of Necessity) እና በአስቸኳይ ግዜ ህግ መርህ(State of Emergency law or Necessity) መሰረት የሀገራቸውን ህገ መንግስት ለመተርጎም ስልጣን ለተሰጣቸው ፍርድ ቤቶች ጥያቄያቸውን በማቅረብ አራዝመዋል።

በኢትዮጵም በህገ መንግስቱ አንቀጽ 84(1) መሰረት ህገ መንግስታዊ ጉዳዮችን የማጣራት እና ህገ መንግስቱን ተርጉሞ የውሳኔ ሀሳብ ለፌደሬሽን ም/ቤት የማቅረብ ስልጣን ያለው የህገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ነው። ህገ መንግስታዊ ትርጉም እና ውሳኔ የመስጠት ስልጣን ያለው ደግሞ የፌደሬሽን ም/ቤት ነው። ሥለዚህ ምርጫና የመንግስት ቀጣይነትን አስመልክቶ ህገ መንግስቱ ምን ይላል፤እንዴትስ መተርጎም አለበት የሚሉት ነጥቦች ከህገ መንግስቱ አንጻር በምክር ቤቱ እንዲተረጉሙ መጠየቁ ተገቢ ነው እንላለን።

በህገ መንግስቱ አንቀፅ 54(1) መሰረት የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባላት ሁሉ አቀፍ፤ ነፃ፤ ቀጥተኛ፤ ትክክለኛ በሆነና ድምፅ በሚስጥር በሚሰጥበት ሥርዓት በየአምስት ዓመቱ በህዝብ እንደሚመረጡ ይደነግጋል።አንቀጽ 58(3) ደግሞ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚመረጠው ለአምስት አመታት ነው፤ የስራ ዘመኑ ከማብቃቱ አንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል ይላል።የክልል ህገ መንግስታትም ተመሳሳይ ድንጋጌዎችንአካተዋል። በዚህ ህግ መሰረት የምክር ቤቱ የስራ ዘመን አምስት ዓመታት ሲሆን የሚጠናቀቀው ደግሞ አዲስ ምርጫ በማካሄድ ነው። ነገር ግን አምስት ዓመቱ መጠናቀቂያ ላይ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አዲስ ምርጫ ባይካሄድ ውጤቱ ምን ይሆናል ለሚለው ጥያቄ ግልጽ ምላሽ የለውም። ከዚህ ህግ የምንረዳው የምክር ቤቱ የስራ ዘመን ተጠናቀቀ እንዲባል አዲስ ምርጫ መደረግ ቅድመ ሁኔታ መሆኑን ሲሆን አዲስ ምርጫ ካልተደረገ የምክርቤቱ የስራ ዘመን ዓምስት ዐመት ቢሆንም እንዳልተጠናቀቀ እንደሚቆጠር ነው።ነገር ግን ምርጫ ሊራዘምባቸው የሚችልባቸውን ምክንየቶች በጠባቡ በግልጽ አለመደንገጉ ለትርጉም የተጋለጠ ማድረጉ አልቀረም። አምስት አመቱ መጠናቀቂያ ላይ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አዲስ ምርጫ ባይካሄድ ውጤቱ ምን ይሆናል ለሚለው ጥያቄም ግልጽ ምላሽ የለውም። በያዝነው ጉዳይ የምርጫ ዝግጅትና ምርጫ ለማካሄድ ያልተቻለው በአስቸኳይ ጊዜ ምክንያት የህዝብ ጤና እና ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል አለም አቀፍ ወረርሽኝ በመከሰቱ ነው። ስለዚህ ከላይ የተገለጸውን ምርጫን የሚመለከት ህግ ከአስቸኳይ ግዜ ህግ ጋር አጣምሮ መተርጎም አስፈላጊ ነው።

### 5.3. የኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ 93

በአንቀጽ 93(ሀ) መሰረት የህዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የአስቸኳይ ግዜ አዋጅ ለመደንገግ እንደሚቻል በግልጽ ተደነግጓል። የወረርሽኙ ባህሪ፤ አለምአቀፋዊ ይዘት እና በመንግስታት የተወሰዱ እርምጃዎች ከላይ ተዳሰዋል። የሚንስትሮች ም/ቤት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 93(4) መሰረት የህገ መንግስቱን አንቀጽ 54፤ 58 እና 38ን ለማገድ ይችላል። ይህንን

[34]International Foundation for Electoral System

ከዚህም በተጨማሪ ምርጫን ለማስፈጸም ሀላፊነት ያለባቸው የመንግስት አካላትን ማየት ያስፈልጋል። የህግ አውጭውና ህግ አስፈጻማው እንዲሁም ገለልተኛ የሆነው የምርጫ ቦርድ ምርጫውን በህገ መንግስቱ በተቀመጠው ግዜ ውስጥ የማከናወን ግዴታቸውን መወጣታቸውን መመርመር ያስፈልጋል። ከላይ እንደተዘረዘረው ምርጫውን ለማከናወን ዝግጅት እየተደረገ የነበረ ሲሆን ምርጫ ቦርድም ምርጫው የሚካሄድበትን ግዜ አሳውቆ ነበር። ነገር ግን ምርጫውን ለማከናወን በዝግጅት ላይ እያለየፌደራል መንግሥቱና እና አንድ ክልል የአስቸኳይ ግዜ አዋጅ አውጀዋል። በነዚህ የአስቸኳይ ግዜ አዋጆች መሰረት ምርጫን ለማከናወን መሰረታዊ የሆኑ እንደ መሰብሰብ፤ መወያየት እና ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ የመሳሰሉት መብቶች መታገዳቸው በሽታውን ለመከላከል አስፈላጊ እርምጃ መሆኑ በሳይንስም የተረጋገጠ ስለሆነ ገደብ ተጥሎባቸዋል።

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ አንቀጽ 54(1)፣ 58(3) እና 38ን በግልጽ ጠቅሶ ሳያግድ ነገርግን ለእነዚህ ድንጋጌዎች መሠረታዊ የሆኑትን ሌሎች መብቶችን በጠቅላላው በመገደቡ ለክርክር በር መክፈቱ አልቀረም። አሁን በሥራ ላይ ጸንቶ ያለው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የታወጀው ለአምስት ወራት ብቻ ሲሆን ወረርሽኙ በዚህ ጊዜ ውስጥ ባይገታ ሕግ አውጪው አካል የሚኖረው ቀሪ ዕድል አንድ ብቻ ሲሆን ይሄውም በቀረችው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ አዋጁን ለአንድ ተጨማሪ አራት ወራት አራዝሞ የስራ ጊዜውን ማጠናቀቅ ነው የሚል ክርክር ሊቀርብ ይችላል። ሆኖም አዲስ ምርጫ ባልተደረገበት ሁኔታና ወረርሽኙም በተጨማሪው ጊዜ ካልተወገደ አገር የመምራት ኃላፊነቱ የማን ሊሆን ይችላል የሚለውን ጥያቄም የሕገ መንግሥቱ 93 በግልጽ አይመልስም። በዚህ ጊዜ ውስጥ የታወጀውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አተገባበር እንዲሁም የስራ አስፈጻሚውን ሥራ በአጠቃላይ የሚከታተለው እና የሚከታተለው አካል ማን ሊሆን ይችላል የሚለውንም 93ን በመተርጎም ካልሆነህጉ በግልጽየሚናገረው ነገር የለም። ነገር ግን ከአንቀጽ 55(8)፤ 93(2)፤ 93(3)(ሀ) እና(5) የምንረዳው በአስቸኳይ ግዜ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት በስራ ላይ መሆን እንዳለበት ነው።

የአስቸኳይ ግዜ አዋጅ መሠረታዊ ባህርይ በተለየ ሁኔታ ስልጣን እና ሀብት በአስፈጻሚው የመንግስት አካል የሚከማችበትና መሠረታዊ የሰብአዊ መብቶች የሚገደቡበት ሥርዓት መሆኑ ነው። ይህንን ሥርዓት ከመደበኛው ጊዜ በተለየ ሁኔታ የህግ አውጭው አካል ካልተቆጣጠረ አስፈጻሚው አምባገነን ሊሆን ይችላል የሚል እምነት አለ።ለዚህም መፍትሄ ይሆን ዘንድ ህግ አውጪውና ህግ ተርጓሚው ተጠናክረው በአስፈጻሚው ላይ ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ አለባቸው።በአጠቃላይ በአስቸኳይ ግዜ ከመደበኛው ግዜ በተሸለ ሁኔታ የደሞክራሲ ተቋማት ተጠናክረው ስራቸውን መስራት አለባቸው። ለፌደሬሽን ም/ቤት ቀጣይነት ብቸኛው ምክንያትም ይህ ይመስላል። ምክንያቱም የፌደሬሽን ም/ቤት በህዝብ ሊመረጥ ወይም በክልል ም/ቤቶች የሚላኩ አባላትን የሚይዝ[35] ሲሆን እስካሁን ባለው ልምድ የፌደሬሽን ም/ቤት አባላት በክልል ም/ቤቶች የሚላኩ ናቸው። ስለዚህ የመደበኛ ምርጫ መደረግ እና አለመደረግ በቀጥታ የሚመለከታቸው አይደሉም። ም/ቤቶቹ እየተሰበሰቡ ስለሆነ በወረርሽኙ ምክንያት የክልል ም/ቤቶች እነዚህን ሠዎች መርጠው ለመላክ አይችሉም ብሎ ለመከራከርም ያስቸግራል። ከዚህም በተጨማሪ ህገ መንግሥቱ የም/ቤቱ የስራ አምስት አመት[36] መሆኑን ከመግለጽ በስተቀር አምስት ዐመቱ የሚጠናቀቀው አዲስ ምርጫ በማድረግ ነው አይልም። ስለዚህ ም/ቤቱ በህግ ተርጓሚ ሚናው እንደ እና ክልል ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን አደጋ ላይ ሲጥል በሚኖረው ሚና እንደተቆጣጣሪ ካልተቆጠረ በስተቀር ስልጣኑ ከአምስት ዐመት የሚረዝምበት ጠንካራ ምክንያት የለም። የዚህ ም/ቤት አባላት በህዝብ ያልተመረጡ መሆን፤ ህግ የመተርጎም ትምህርት እና ልምድ ማነስ፤የቁጥራቸው መብዛት፤የስብሰባ ጊዜያቸው

አስፈጻሚ እና ህግ አውጪ አባላት መሆናቸው የገለልተኝነት እና ብቃት እንዲሁም ተገቢነትጥያቄ እንዲነሳ ያደርጋል። ነገር ግን አሁን በህግ ስልጣን የተሰጠው የህገ መንግስት ተርጓሚ አካል በመሆኑ እና በአስቸኳይ ጊዜ ውስጥ ሊነሱ የሚችሉ የህገ መንግስት ክርክሮችን አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው በመሆኑ ከመቀጠሉ ውጭ አማራጭ የለም። በተጨማሪም የክልል ም/ቤቶቹ የስልጣን ዘመን ካለፈ እና በአስቸኳይ ግዜ ላይ እያሉ የፌደሬሽን ም/ቤት አባላትን መልምለው ቢልኩ ህጋዊነት ይጎድለዋል።

በአጠቃላይ በህገ መንግስቱም፤ በአለም አቀፍ ተሞክሮም፤ አለም አቀፋዊ ተቀባይነት ባለው የአስቸኳይ ግዜ ህግ ፍልስፍና መሰረትም በአስቸኳይ ግዜ የመንግስተ ቀጣይነት መረጋገጥ አለበት። ጀርመን፤ ሀንጋሪ እና ፈረንሳይ ደግሞ ይህንኑ በህገ መንግስታቸው ላይ በግልጽ ካሰፈሩት ሀገራት ለአብነት የሚጠቀሱ ሲሆን ሌሎች ደግሞ ህጋቸውን በመተርጎም የመንግስታቸውን ቀጣይነት ያረጋግጣሉ። በመሆኑም ሕገመንግሥቱ ህግ አውጭ የሌለበት የአስቸኳይ ጊዜን ታሳቢ አያደርግም። ይህንን የሚያሳይ ድንጋጌም የለውም። ይህም ሁኔታ ለሕገ መንግስቱ መተርጎም ሌላው ምክንያት ነው የሚል እምነት አለን።

### 6. ጊዜን በሚመለከት ለተነሳው ጥያቄ

ለጉባኤው የቀረበው ሁለተኛ ጥያቄ ከጊዜ ጋር የሚያያዝ ሲሆን “ምርጫው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ እንዲታወጅ ምክንያት የሆነው ክስተት ከተወገደ በኋላ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ሊከናወን ይገባል?” የሚል ነው። ለአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ መታወጅ ምክንያት የሆነው በዓለምና በአገራችን የተከሰተው ኮቪድ19 የተባለው ወረርሽኝ መድኃኒት ተገኝቶለት ወይም በሌላ በማንኛውም መልኩ በቁጥጥር ሥር ቢውልና ችግር መሆኑ ቢቀር የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁንም ቀሪ እንደሚያደርገው እርግጥነው። ዋናው ጥያቄ ግን ችግሩ ከተወገደና የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ቀሪ ከሆነ በኋላ ምርጫው በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ሊከናወን ይችላል የሚለው ነው። በተከሰተው አለም አቀፋዊ ወረርሽኝ ምክንያት የአስቸኳይ ግዜ አዋጅ በህገ መንግስቱ መሰረት ከመታወጁም በላይ በዚህ አዋጅ ሕገ-መንግሥተዊነት ላይ የተነሳ ክርክር የለም። የመምረጥ እና የመመረጥ መብት በጊዜያዊነት በአንቀጽ 93(4) መሰረት በአስቸኳይ ግዜ አዋጅ ሊታገዱ ከሚችሉ መብቶች ውስጥ መሆናቸው አላከራከረም። በኮቪድ19 ወረረሽኝ ምክንያት በሌሎች አገራትም ከላይ እንደተገለጸው በርካታ ምርጫዎች እንዲራዘሙ ተደርጓል። ይህንንም ክዶ የሚከራከር ወገን የለም። ምርጫን በገለልተኛነት ለማስፈጸም በህገ መንግስቱ ስልጣን የተሰጠው የምርጫ ቦርድ ምርጫ ለማካሄድ እደማይችል አስቀድሞ ያሳወቀ መሆኑ ፤ ምርጫውን በተያዘለት ግዜ ማድረግ የህዝብን ጤና እና ደህንነት ለአደጋ እንደሚያጋልጥ በመረጋገጡ፤ በመግቢያው ላይ እንደተገለጸው የህገመንግስቱ ዓላማም የህዝብን ጤና እና ደህንነት በምርጫ ምክንያት ለአደጋ ማጋለጥ ባለመሆኑ ምርጫውን የሚመለከቱት ከላይ የተገለጹት አንቀጾች በአስቸኳይ ግዜ ምክንያት ታግደው ምርጫው ለተወሰነ ግዜ መራዘሙ ህገ መንግስታዊ ነው እንላለን።

መሰረታዊ የህገ መንግስት ትርጓሜ አስተሳሰቦችንም በመከተል ህገ መንግስቱን ያጸደቁት/ያረቀቁት ሰዎች “አዲስ ምርጫ ተደርጎ የምክር ቤቱ የሰራ ዘመን ይጠናቀቃል” ያሉበትን መንፈስ ብንመረምር መልሱ የመንግስትን ቀጣይነት ማረጋገጥ ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ አምስት አመቱ ሲጠናቀቅ የምክርቤቱ የስራ ዘመን ይጠናቀቃል ብለው ይደነግጉ ነበር። ይህም በህገ መንግስቱ መግቢያ ላይ ከተገለጸው እና ከአጠቃላዩ የህገ መንግስት ዓላማም ጋር የተስማማ ነው። በአስቸኳይ ግዜ የህግ አውጪው አካል መስራት የሚገባውን ለይተው በግልጽ ህግ መደንገጋቸውም በአስቸኳይ ግዜ የመንግስትን ተጠናክሮ መቀጠልን ታሳቢ አድርገው ነው።

በዘመናዊ/ተራማጅ የህገ መንግስት አተረጓጎም መርህም ቢሆን ህገ መንግስቱን የቀረጹት ሰዎች ዛሬ ላይ የተከሰተውን ወረርሽኝ ቢያዩት የአስቸኳይ ግዜ አዋጅ ማወጃቸው፤ምርጫውን ማራዘማቸው እና የመንግስትንም ቀጣይነት ማረጋገጣቸው አይቀሬ ነው። ከላይ እንደገለጽነው የምክር ቤቱ የስራ ዘመን ተጠናቀቀ የሚባለው አዲስ ምርጫ ሲካሄድ ነው። በአስቸኳይ ግዜ ምክንያት አዲስ ምርጫ ለማድረግ ስላልተቻለ ምርጫው መራዘሙ የግድ ነው። የአስቸኳይ ግዜ አዋጅም ታውጇል። ሥለዚህ ምርጫ ሳይካሄድ የምክርቤቱ ዘመን ተጠናቋል ማለት አይቻልም። በህገ መንግስቱ መሰረትም በአስቸኳይ ግዜ የመንግስት ቀጣይነት መረጋገጥ አለበት። የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ለማወጅ ምክንያት የሆነውን ወረርሽኝ መቆጣጠር እና አዲስ ምርጫ አድርጎ የምክር ቤቱን የስራ ዘመን ማጠጠናቀቅ እስኪቻል ድረስ የመንግስት ቀጣይነትን ማረጋገጥ ህገመንግስታዊ ግዴታ ነው።

የምርጫ ቦርድ የጊዜ ሰሌዳ እንደሚያስረዳው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ የታወጀው የምርጫ ዝግጅት አድርጎ ምርጫውን ለማከናወን ስድስት ወራት ሲቀሩት ነው። ምንም እንኳን በተጣበበ የጊዜ ሰሌዳ ቢሆንም ምርጫውን በነሃሴ ወር 2012 ለማካሄድ ምርጫ ቦርድ የጊዜ ሰሌዳ አውጥቶ እንደነበር ይታወቃል። ከእነዚህ ሁኔታዎች በመነሳት ኮቪድ19 በወረርሽኝ ደረጃ የአገራችን የጤና ስጋት መሆኑ ማብቃቱ ተረጋግጦ በፌደራልና በክልል መንግሥታት የወጡ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጆች ቀሪ መሆናቸው ከተረጋገጠበት ጊዜ አንስቶ **ከስድስት እስከ ዘጠኝ ወር** ባሉት ጊዜያት ውስጥ ወይም የምርጫ ቦርድ በሚያቀርበው የአጠረ የጊዜ ሰሌዳ መሠረት አገራዊና ክልላዊ ምርጫዎቹ እንዲካሄዱ እንዲሁም የምርጫ ውጤቱ በታወቀ **በሁለት ወራት** ጊዜ ውስጥ አሁን በሥራ ላይ ያለው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሥልጣን እንዲያበቃ ተደርጎ የህገ መንግሥቱ አንቀጽ 58(3) ሊተረጎም ይገባዋል እንላለን።

**ማጠቃለያ**

1. የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 54(1)፣ አንቀጽ 58(3) እና አንቀጽ 93 አሁን ሃገሪቱ የገጠማትን ያልታሰበ ችግር ሊፈታ በሚችል መልኩ ምሉዕ ሆነው የተቀረጹ ባለመሆናቸው ትርጉም እንዲሰጥባቸው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጠየቁ ተገቢ ነው እንላለን።
2. ለእነዚህ ድንጋጌዎች የሚሰጠው ትርጉም አሁን በሥልጣን ላይ ያለው ምክርቤት፤ ሥራ አስፈፃሚ እና ሌሎች የደሞክራሲ ተቋማት የኮቪድ19 ችግር ተወግዶ ምርጫ እስኪደረግና ውጤቱ እስኪታወቅ ድረስ ሊቀጥሉ እንደሚችል ሊያመላክት ይገባዋል።
3. በሚሰጠው ትርጉም ላይ ወረርሽኙ መወገዱ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በሳይንሳዊ መንገድ ማረጋገጫ ከተሰጠ እና አስቸኳይ ግዜ አዋጁ ቀሪ ከሆነ በኋላ ምርጫው ከስድስት እስከ ዘጠኝ ወር ባሉት ጊዜያት ውስጥ ወይም የምርጫ ቦርድ በሚያቀርበው የአጠረ የጊዜ ሰሌዳ መሠረት እንዲካሄድ እንዲሁም የምርጫ ውጤቱ በታወቀ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ አሁን በሥራ ላይ ያለው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሥልጣን እንዲያበቃ ተደርጎ የህገ መንግሥቱ አንቀጽ 58(3) ሊተረጎም ይገባዋል እንላለን።

----------/////////----------